# Learning by Ear 2013

"መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ "መዘዙን መቀበል"

EPISODE 20: የድሉ መዝሙር

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, Maja Braun, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: ምህረት ASKS አልማዝ FOR HELP**

- ምህረት **(F, 15)**
- አልማዝ **(F, 16)**

**SCENE 2: THE STUDENTS RESCUE ትዕግስት**

- ምኞቴ **(M, 35)**
- ትዕግስት **(F, 15)**
- በለጠ **(M, 16)**
- **MALE STUDENT (M, 16)**
- አልማዝ **(F, 16)**
- ምህረት **(F, 15)**
- **5 STUDENTS (M/F)**

**SCENE 3: ዳንኤል COMES BACK TO BONGO ACADEMY**

- ዳንኤል **(M, 16)**
- **GUARD (M, 60)**

- **በለጠ (M, 16)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **አልማዝ (F, 15)**
- **5 STUDENTS (M/F)**

## INTRO

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ "መዘዙን መቀበል"የተሰኘዉ ሁለተኛ ዙር ድራማ ነዉ። ስለ ምህረት አልማዝ እና ሌሎቹ ታዳጊ ወጣቶች ለማወቅ እንደተዘጋጃችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ዛሬ የሚቀርበዉን ድራማ ሃያኛ ክፍል ከመጀመራችን በፊት ግን እስከአሁን የተከናወነውን መለስ ብለን እናስታውስ...ምህረት ነፍሰ ጡር በመሆኗ ከትምህርት ቤት ከተባረረች በኋላ የተወሰኑ ጥብቅ ቅድመ ሁኔታዎችን በማሟላትዋ ወደ ቦንጎ አካዳሚ እንድትመለስ ተፈቅዶላታል፡፡ እዚያም ከጎረቤት ሀገር ላቦሪያ በልውውጥ ትምህርት መረሃ-ግብር ከመጣችው ተማሪ አልማዝ ጋርተዋዉቃለች፡፡ ታዲያ ሁለቱ ሴቶች አንድ የሚያደርጋቸው የሆነ ነገር እንዳለም ወዲያውኑ ይረዳሉ።

## 2. EPISODE 19, LINES 74 – 75:

<u>አልማዝ:</u> እውነት ለመናገር ዳንኤል ሁለታችንንም ክዶናል፡፡ ስሚኝ ምህረት ስሚኝ፤ በጣም አዝናለሁ፡፡ በአንቺ ላይ እንደዛ ክፉ በመሆኔ አዝናለሁ፡፡ ቀንቼ ነው፣

<u>ምህረት:</u> ኦህ አልማዝ-ምንም አይደለም፡፡ እውነት ለመናገር ተረድቼሻለሁ፡፡ የወንድ ጓደኛሽ እንዳታለለሽ ስትረጂ ምን እንደሚሰማሽ ይገባኛል፣. *(They laugh)a*

**3. NARRATOR:**

የአልማዝ የቀድሞ ፍቅረኛ እና ያልተወለደው የምህረት ልጅ አባት፣ ዳንኤልም ከትምህርት ቤት ተባሮ ነበር። ዘግይቶም ቢሆንወደ ትምህርት ቤቱ ያልተመለሰ አንድ ሰውም አለ። ከሌሎቹ ተማሪዎች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ትማር የነበረችውና በእድሜ ወደሚበልጣት የወንድ ጓደኛዋ ምኞቴ ጋር ጠቅልላ የገባችው ትዕግስት። ትዕግስት ትምህርት ቤት ባለመምጣቷ ምህረት ስለተጨነቀች ልትፈልጋት ሄዳም ነበር።

**4. EPISODE 19, LINES 110 – 111:**

<u>ምህረት</u>: ትዕግስት፣ ብቻሽን ነሽ? በሩን የቆለፈው ማን ነው? ምን እየሆነ ነው ነገሩ?

<u>ትዕግስት</u>: ምኞቴ አብዷል! እዚህ ቆልፎ አስቀምጦኛል! እንድወጣ አይፈልግም።

**5. NARRATOR:**

እስኪ ምህረትን ከዚህ አስደንጋጭ ግኝቷ በኋላ “የድል መዝሙር” በተሰኘው የድራማ ሃያኛ ክፍል ላይ እናግኛት።

## <u>SCENE 1: ምህረት ASKS አልማዝ FOR HELP</u>

**6. ATMO: INSIDE BONGO ACADEMY, AFTER SCHOOL, CORRIDOR OUTSIDE GIRLS’ DORMITORIES**

**7. SFX: URGENT KNOCK ON DOOR**

**8.** ምህረት: **(panting, desperate)** አልማዝ! እባክሽን ክፈቺ!

**9.** አልማዝ: **(from inside)** ማን ነው?

**10.** ምህረት: **(shouts)** እኔ ነኝ ምህረት! ክፈቺ።

11. **SFX: FLIPFLOPS APPROACHING ON OTHER SIDE OF DOOR**

12. **SFX: DOOR OPENS**

13. አልማዝ: ምህረት፣ ምን እያደረግሽ ነው? ወደ ቤት የሄድሽ መስሎኝ ነበር!

14. ምህረት: ልትረጂኝ ይገባል፡፡ ትዕግስት ችግር ላይ ናት፡፡ ማን አብሮኝ እንደሚሄድ አላወቅኩም

15. አልማዝ: እስቲ ረጋ በይ ፣ ምህረት፡፡ ምን ተፈጠረ?

***KW BEGIN***

16. ምህረት: **(catching her breath)** I… I…

17. አልማዝ: ደግሞ ላብ በላብ ሆነሻል! ከ ትምህርት ቤት እዚህ ድረስ ስትሮጪ ነው እንዴ የመጣሽው?

18. ምህረት: ይህን የተቀፈደደ ሆድ ተሸክሜ መሮጥ አልችልም፡፡ ግን የቻልኩትን ያክል ፈጥኜ ተራምጃለሁ፡፡

19. አልማዝ: ምህረት፣ ከዚህ በላይ መንቀሳቀስ የለብሽም፣ ታውቂያለሽ፣ ሁኔታሽን

20. ምህረት: **(cuts in)** አልማዝ፣ ስለዚያ በኋላ እናወራለን! አሁን ትዕግስትን ልንረዳት ይገባል!

21. አልማዝ: እሺ፡፡ ምን እንደተፈጠረ ንገሪኝ!

***KW END***

22. ምህረት: **(still panting)** ወደ ትዕግስት ቤት ሄድኩኝ እና ጎረቤቷ ምኞቴ ጋር እንደሆነች ነገረችኝ፡፡ ከእዝያ ትምህርት ቤት ለምን እንዳልመጣች ልጠይቃት ሄድኩ-

23. አልማዝ: **(interrupts her)** ሄይ! ሄይ፣ ምህረት፣ ቆይ-አልገባኝም! ምኞቴ ማን ነው?

**24.** ምህረት:የሆነ የታክሲ ረዳት ነው። ፍቅረኛዋ...ወይም የቀድሞ ጓደኛዋ... እኔ እንጃ። የሆነ ጊዜ ላይ አብረው መኖር እንዲጀምሩ ጠይቋት ነበር እና፣ ታደርገዋለች ብዬ አስቤ አላውቅም... **(pulls herself together),,,,** ለማንኛውም የሚኖርበትን ቤት አገኘሁት ግንሰው ያለበት አይመስልም ነበር። ከእዛ ልክ ልመለስ ስል የሆነ ሰው ስሜን ሲጠራኝ ሰማሁ። የጠራችኝ ትዕግስት ነበረች። ምኞቴ ያለ ፈቃዷ ቤቱ ዉስጥ ቆልፎ አስቀምጧታል! ከውጪ ቤቱን ቆልፎባታል!

**25.** አልማዝ: ምን? ቆይ ጫማዬን ላድርግ። ርዕሰ መምህርት ሰብለን ማግኘት አለብን።

**26.** ምህረት: እሳቸዉ የሉም። ሄጄ ነበር።

**27.** አልማዝ: ጥሩ፤ ብቻችንን መሄድ አንችላለን። ወደ ወንዶቹ ማደሪያ ክፍል ሂጂና የቻልሽውን ያህል ተማሪዎች ጥሪ። እኔ ጫማዬን ላድርግና እዚህ ፎቅ ላይ ያሉትን ሴቶች ቀስቅሼ ትምህርት ቤቱ መግቢያ በር ላይ እንገናኛለን። እሺ?

**28.** ምህረት: እሺ፤

**29. SFX: FLIPFLOPS AS አልማዝ RUNS INSIDE**

**30. SFX: FOOTSTEPS WITH SHOES AS ምህረት RUNS AWAY IN OPPOSITE DIRECTION**

**31. MUSICAL INTERLUDE**

## SCENE 2: THE STUDENTS RESCUE ትዕግስት

**32. SFX: AT ምኞቴ INSIDE**

**33.** ትዕግስት: **(cries, sniffles) (to herself)** መቼም ምህረት እኔን የምትረዳበት መንገድ እንደምታገኝ ተስፋ አለኝ! እንዴት እንዲህ አይነት ችግር ውስጥ ገብቼ እቀራለሁ? ከምኞቴ ጋር ወደ ቤቱ መምጣት አልነበረብኝም!

**34.** ምኞቴ: **(drunk, from other room)** ዉቢትዋ ትዕግስት ነይ እዚህ ጋር! እርቦኛል፡፡ ለሁለታችንም ምግብ መስራት አለብሽ!

**35.** ትዕግስት: **(sniffles)**

**36.** ምኞቴ: ትዕ...ግስት...ትዕግስት ወደ ምኞቴ ነይ!

**37.** ትዕግስት: **(to herself)** ተው፣ እባክህን ተወኝ......

**38.** ምኞቴ: **(shouts)** እዚህ ጋር ነይ ብያለሁ፡፡ ድንጋይ ራስ!

**39.** ትዕግስት: **(startled, cries)** እሺ ...እሺ...!

**40. SFX: SLOW FOOTSTEPS AS SHE APPROACHES**

**41.** ምኞቴ: **(calmer)** ሳሚኝ፡፡

**42.** ትዕግስት: **(cries as they kiss)**

**43. SFX: KISSING**

**44.** ምኞቴ: **(tender)** የእኔ ውድ ትንሿ ሚስቴ ሁል ጊዜ እንድበሳጭ ለምን ታደርጊኛለሽ?

**45.** ትዕግስት: **(crying)** ምኞቴ፣ ወደ ቤት መሄድ እፈልጋለሁ......

**46.** ምኞቴ: አሀ፣ አታልቅሺ፣ የእኔ ቆንጆ፡፡ እባክሽን አታ...--

**47. SFX: GLASS BREAKS AS STONE HITS WINDOW**

**48. SFX: ATMO FROM OUTSIDE GETS LOUDER (LIGHT TRAFFIC)**

**49.** ምኞቴ: **(shouts)** ሄይ! ማን ነው እንዲህ ያደረገው?

**50.** በለጠ: **(laughs cheekily from outside)** እኔ! ከቻልክ ግጠመኝ!

**51.** ምኞቴ: **(shouts)** ሄይ፣ አንተ ልፍስፍስ፣ መስኮቴን ሰብረህ ማምለጥ የምትችል ይመስልሀል?

**52.** በለጠ: **(from outside)** አንተ ቦቅቧቃ ምን ልታደርግ ትችላለህ!

**53.** ምኞቴ: ቦቅቧቃ የምትለው ማንን ነው? ለመሆኑ አንተ ማን ነህ? ጠብቀኝ! አሁኑኑ እወጣልሀለሁ! ከእዛም ቦቅቧቃው ማን እንደሆነ አሳይሀለሁ!

**54. SFX: ምኞቴ FOOTSTEPS ON BROKEN GLASS**

**55. SFX: DOOR OPENS**

**56. SFX: TRAFFIC ATMO LOUDER**

**57.** በለጠ **(from a distance)** ና ውጣ ቦቅቧቃ፣ ና ይዋጣልን!

**58. SFX: FOOTSTEPS LEAVE AS ምኞቴ RUNS AFTER HIM**

**59.** ምኞቴ: **(as he runs away)** ጠብቀኝ እይዝሀለሁ፣ አንተ ወጠጤ!

**60. SHORT MUSICAL INTERLUDE**

**OR CHANGE OF AMBIANCE TO OUTSIDE (MORE TRAFFIC)**

**61. SFX: ATMO OUTSIDE THE HOUSE (LIGHT TRAFFIC)**

**62. SFX: RUSTLING OF LEAVES / TWIGS AS STUDENTS HIDE**

**63. አልማዝ:** **(low voice)** እሺ፣ በለጠ እና ምኞቴ በእዛ በጠርዙ በኩል እየተሯሯጡ አልፈዋል፡፡ በለጠ በጣም ፈጥኖ ያመልጣል የሚል ተስፋ አለ ብለን እናስብ

**64. MALE STUDENT:** አትጨነቂ በለጠ ፈጣን ነው!

**65.** አልማዝ: እሺ ፍጠኑ! እንግባ!

**66. SFX: MANY FOOTSTEPS AS STUDENTS ENTER**

**67.** ምህረት: ትዕግስት! ደህና ነሽ?

**68. GIRLS/BOYS:** ምን ተፈጠረ?/ ደህና ነሽ/ ትዕግስት! (ወ.ዘ.ተ)

**69. ትዕግስት:** **(cries)** ምህረት! መጣሽ! ሁላችሁም መጣችሁልኝ! አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ!

**70.** አልማዝ: ተነሽ፣ ከዚህ ይዘናት መውጣት አለብን፡፡ ጥያቄዎቹ ለበኋላ ይቆዩን!

***KW BEGIN***

**71. ትዕግስት:** ምህረት፣ ያቺ ልጅ ማን ናት?

**72. ምህረት:** አልማዝ ነች፡፡ ችግር የለውም፣ ልታምኛት ትችያለሽ፡፡

**73. አልማዝ:** ሄይ፣ ጥያቄ በኋላ ብያለሁ፡፡ ፍጠኑ!

***KW END***

**74. SFX: COMMOTION, FOOTSTEPS AS THEY ALL LEAVE**

**75. SFX: POLICE SIREN APPROACHING**

**76.** አልማዝ: እሰይ፣ ጥሩ፡፡ ፖሊሶቹ መምጣታቸዉ ጥሩ ነው፡፡ ያደረግነው ትክክለኛ ነገር ነው መደወላችን በጀ,,,

**77. MUSICAL INTERLUDE**

**SCENE 3: ዳንኤል COMES BACK TO BONGO ACADEMY**

**78. ATMO: BONGO ACADEMY, EXTERIOR, EVENING. CRICKETS, LIGHT TRAFFIC**

**79. SFX: NOISE OF TROLLEY BAG BEING PULLED**

**80. SFX: FOOTSTEPS ዳንኤል - STOP**

**81. SFX: KNOCKS ON IRON GATE (BONGO ACADEMY)**

**82.** ዳንኤል: **(calls)** ሄሎ? ጥበቃ?

***KW BEGIN***

**83. SILENCE**

**84. SFX: KNOCKS ON IRON GATE**

**85.** ዳንኤል: ሰሙኝ እዛ ጋር ሰው አለ? **(to himself)** ምን አይነት አስጠሊታ ነገር ነዉ፡፡ ይህ ሰውዬ አንድ ቀን የትምህርት ቤቱ በር ላይ ተገኝቶ አያውቅም ፡፡ ርዕሰ መምህርት ሰብለ ይህንን ሰውዬ ለምን እንደማታባርረው አይገባኝም፡ ፡ ለነገሩ እኔ ን ምን ቸገረኝ፣ ዝም ብዬ እገባለሁ፡፡ አጎቴ ደብዳቤውን ቀድሞ ሰጥቶኝ ቢሆን ኖሮ  ይሄኔ ሳልዘገይ በጠዋት ትምህርት ቤት በገባሁ ነበር…

***KW END***

**86. SFX: IRON GATE BEING PUSHED OPEN**

**87. SFX: FOOTSTEPS AND TROLLEY AS ዳንኤል ENTERS**

**88. GUARD:** **(from far)** ሄይ፣ ስማ! ቁም! ሌሊቱን ከትምህርት ቤት ዘልለው ከወጡት ተማሪዎች መሀከል አንዱ ነህ?

**89.** ዳንኤል: **(confused)** ዘለለክ? እ…አልገባኝም።.

**90. GUARD:** **(closer)** ብልጥ አትሁን። ጥቂቶቻችሁ ጠፍታችሁ እንደነበር አውቃለሁ። አንተም አንዱ ነህ! ስምህ ማን ነው?

**91.** ዳንኤል: ስሜ ዳንኤል ነው። ከትምህርት ቤት ተባርሬ ነበር። ወደ ትምህርት ቤት እንድመለስ ደብዳቤ ደርሶኛል። ግን በማርፈዴ ይቅርታ።

**92. GUARD:** **(realizing)** አሀ! ዳንኤል ካሳሁን?

**93.** ዳንኤል: እዎ

**94. GUARD:** እሺ፣ ወ/ሮ ሰብለ ነግረዉኛል። የድሮ ክፍልህን ቁልፎችም ሰጥተዉኛል። ይውልህ ውሰድ።

**95. SFX: KEYS JINGLE**

**96.** ዳንኤል: አመሰግላሁ ጥበቃ። እ…

**97. STUDENTS** **(from a distance, singing song of victory while moving closer)** አንበሳው ጋሜ ነብር ነው ወይ!

አንበሳው ጋሜ!

**98. OTHER STUDENTS:** **(from far)** ትዕግስት! ትዕግስት!

**99. GUARD:** ኧረ ምንድን ነው! በጥባጮቹ ተማሪዎች! ምንድን ነዉ እንዲህ ያስደሰታቸው? እዩ! ለወ/ሮ ሰብለ እንደነገርኩባቸው አላወቁም?

**100. STUDENTS:** **(still singing, closer)**

101. ዳንኤል: የስፖርት ውድድር ወይም የሆነ ነገር ነበር? የቦንጎን የድል መዝሙር የሚዘምሩ ይመስላል…

102. GUARD: (grumpy) የማውቀው ነገር የለም። (shouts to students) ቁሙ! እያንዳንድሽ በቀጥታ ወደ እኔ ! ስማችሁን ንገሩኝ!

103. STUDENTS: (almost next to guard, stop singing)

104. በለጠ: ጥበቃ ስማ! አንተ ሲጋራህን እያጨስክ ከመሀላችን ተጠልፎ የነበረውን ለማዳን ሄደን ነው! እንግባበት!

105. STUDENTS: (supporting በለጠ) ልክ ነው! በለጠ ልክ ነው! ትዕግስትን አድነን መጥተናል…

106. SFX: COMMOTION AS STUDENTS TRY TO PASS THE GUARD

107. STUDENTS: ዞር በል ጥበቃ! ቶሎ በል መንገዳችንን ልቀቅ!

108. GUARD: (shouts) ሄይ አንተ! በዚህ በር ማንም አይገባም! በዚህ በር ማንም አይገባም ብያለሁ!

109. በለጠ: (surprised) እንዴ ዳንኤል ተመለስክ?

110. ዳንኤል: (uncomfortable) ሃይ በለጠ

111. በለጠ: ኑ ሰዎች እንሂድ! ዳንኤል በኋላ እንገናኛለን።

112. STUDENTS (except for ምህረት and አልማዝ laugh and go inside school compound. They sing again)

113. ምህረት: (coldly) ሃይ ዳንኤል።.

114. ዳንኤል: (stutters) እምም…ሃይ…ም…ምህረት?

***KW BEGIN***

**115.** ምህረት: **(sarcastic)** ውይ ሲደንቅ ! ቢያንስ ስሜንም አልረሳከውም?

**116.** ዳንኤል: **(shocked)** ምህረት! አንቺ ...አንቺ...ሆድሽ......

***KW END***

**117.** አልማዝ: ሃይ፣ ዳንኤል!

**118.** ዳንኤል: **(even more surprised)** አልማዝ? እዚህ ምን ትሰሪያለሽ? ለምን ከላቦሪያ ወጣሽ?

**119.** አልማዝ: አዎ፣ እዛ ብሆን ትመርጣለህ! በልውውጥ የትምህርት መርሃ ግብር እዚህ ትምህርት ቤት ገብቻለሁ።

**120.** ዳንኤል: ምን ማለት ነው? ምህረት እቤት መሆን አልነበረብሽም?

**121.** ምህረት: **(sarcastic)** ውይ፣ ዳኒ ስለ እኔ በመጨነቅህ አመሰግናለሁ! ምንም ችግር የለዉም፥ ፥ ትዕግስትን በማዳናችን አሁን እየተደሰትን ነዉ። አየህ፣ ከአንተ በተቃራኒው እኔስ ከጓደኞቼ ጋር ተሰልፌአለሁ። ሁለታችሁ እንድትነጋገሩ ትቻችሁ ልጂድ። ብዙ እንደምትወያዩ ተስፋ አደርጋለሁ።

**122.** አልማዝ: አይሆንም፣ ምህረት። ቆይ! በዚህ ጉዳይ ላይማ አንድ ነን! **(sarcastic, to** ዳንኤል**)** እና፣ ዳንኤል፣ ንገረን ማወቅ የሚገባን ሌሎች ሴት ጓደኞች የሉህም?

***KW BEGIN***

**123.** ዳንኤል: ም...ምን ማለትሽ ነው?

**124.** አልማዝ: **(angry)** ምን ማለቴ ነው?! እንደምታፈቅረኝ ዋሽተኸኝ ለአንተ ደብዳቤ በመጻፍ እና መልዕክቶችን በመቅረጽ ዌብካም ፊት ለፊት ተገትሬ ስውል አንተ ሆዬ እዚህ ኪሲምባ ውስጥ ሌሎች ሴቶች ልጆችን በማስረገዝ ሰራ ተጠምደህልኝ ነበር! ያን ማለቴ ነው!

**125.** ዳንኤል: እዚህ በህዝብ ፊት ቆመን መወያየት ያለብን አይመስለኝም፣ አልማዝ...እ...

**126.** አልማዝ: እሺ፤ የት እንድንወያይ ፈለግክው? ንገረኝ እስኪ! የት? ምህረት ነፍሰጡር እንደሆነች እና አንተም አባት እንደሆንክ ዓለም ሁሉ ካወቀው በኋላ የት እንድንወያይ ፈለግክ?

**127.** ምህረት: **(agrees)** አሀ!

***KW END***

**128.** ዳንኤል: ይ...ይቅርታ፣ አልማዝ...

**129.** አልማዝ: **(cuts in)** ታውቃለህ? አትረበሸ። **(to** ምህረት**)** ምህረት፣ ነይ እባክሽ እንሂድ!

**130.** ምህረት**:** በደስታ።.

**131. SFX: FOOTSTEPS AS** ምህረት **AND** አልማዝ **LEAVE**

**132.** ዳንኤል**:** **(calls)** አልማዝ፣ ቆይ...ለቦሪያ ውስጥ ነገሮች እንዴት ናቸው? ቤተሰቦቼ እንዴት ናቸው?

**133.** አልማዝ: **(from far)** ደብዳቤ ጻፍላቸው ወይም ደውልላቸው። እኔን አትጨቅጭቀኝ።

**134.** ዳንኤል: **(to himself)**ወይ እግዚአብሔር፣ ምን አይነት መከራ ነው!

**135. GUARD:** ሃሃ! እንኳን ደህና መጣህ!

## 136. <u>OUTRO – NARRATOR:</u>

**እናም…አሁን ሁሉም ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰዋል፡፡ እንዴት አይነት አስደሳች ዳግም መሰባሰብ ይሆን! ሁሉም ሴቶች ስለ ዳንኤል እንደሚያወሩ ካሰባችሁ… ተሳስታችኋል! ትዕግስት በቦንጎ አካዳሚ አልማዝ ክፍል ውስጥ ተቀምጣ ሳለች ምኛቴ ቤት ዉስጥ ምን እንደደረሰባት ግልጽ ሆና ለአልማዝ ነግራታለች፡፡ እስኪ አልማዝ ከምር ምን ታስብ እንደሆን ማወቅ ከፈለጋችሁ የቀረፀችውን የቪዲዮ ዘገባዋን ድረ-ገጻችን ላይ ተመልከቱ ። የድራማውን ያለፉትን ክፍሎች ማድመጥ አልያም ድራማዉን በግል ማህደር መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረ-ገጽ አድራሻችን <u>dw.de/lbe</u> ላይ ያገኛሉ። በፌስቡክ አድራሻችን ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ እስክንገናኝ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።**